## ደንብ ቁጥር ____/2014

## <u>የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

በኢኮኖሚ ምክንያቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65(2) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር __/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/ 2009 (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

   ከደንቡ አንቀጽ 54 (1) (ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (መ) ተጨምሯል፤

   "መ. በሥራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆኑ ሰዎች አዲስ አክሲዮን በመሸጥ የሚያገኙት የፕሪሚየም ገቢ፤"

3. <u>ደንቡ የሚፀናበት ቀን</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ __________ቀን 2014

አቢይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

Samuel Gima Legal Consultant & Attorney

# REGULATIONS NO. ___ /2022

# COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE FEDERAL INCOME TAX REGULATIONS

WHEREAS, for economic reasons it has become necessary to amend the Council of Ministers Federal Income Tax Regulations;

NOW, THEREFORE, the Council of Ministers in accordance with Article 65(2) of the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016, has issued this Regulation.

## 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Federal Income Tax (amendment) Regulations No. ___/2022."

## 2. Amendment

The Council of Ministers Federal Income Tax (as amended) Regulation No. 410/2016 is hereby further amended as follows:

The following new letter (d) is added after Article 54(1) (c) of the Regulation:

"D. premium income obtained by going concern from the sale of new shares to non-residents of Ethiopia;"

## 3. Effective Date

This Regulation shall enter into force from the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa this ______day of ________2022

Ministry of Finance
ARCHIVES
2

Abiy Ahmed ( Dr.)
Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

# በኢትዮጵያ የተቋቋሙ ኩባንያዎች ከሚሸጡት አዲስ አክሲዮን የሚያገኙት ፕሪሚያም በካፒታል ዋጋ ዕድገት ላይ ከሚከፈል ግብር ነፃ እንዲሆን ስለተዘጋጀው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የቀረበ አጭር መግለጫ

## 1. *መግቢያ*

ባለሀብቶች በአንድ አገር ውስጥ ሀብታቸውን ስራ ላይ ለማዋል ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ በካፒታል እጥረት ምክንያት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅማቸውን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ያልቻሉ ኩባንያዎች የሚያወጧቸውን አዲስ አክሲዮኖች ገዝተው የኩባንያዎቹን የካፒታል አቅም እና የአመራረት ዘይቤ በማሻሻል እንዲሁም ባለአክሲዮን በመሆናቸው በኩባንያዎቹ አመራር ውስጥ የመሳተፍ መብት ስለሚኖራቸው የእነዚህን ኩባንያዎች የአመራር አቅም በማሳደግ ምርት እና ምርታማነታቸውን ከፍ ማድረግ እና ከዚህ የሚገኘው ትርፍ ተቋዳሽ መሆን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች በካፒታል እጥረት ምክንያት ነባር የማምረቻ ወይም አገልግሎት የመስጫ መሳሪያዎችን በአዲስ ለመተካት ባለመቻላቸው፤ ዘመናዊ የኩባንያ አመራር እውቀትን መጠቀም ባለመቻላቸው፤ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን በቂ ገንዘብ ስለሌላቸው፤ ለጥሬ ዕቃ መግዣ የሚውል በቂ የውጭ ምንዛሪ የማያገኙ በመሆኑ ወዘተ. አብዛኛዎቹ ከማምረት አቅማቸው በግማሽ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል ከሚያስችሉ እርምጃዎች አንዱ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ባለሀብቶች በተለይም የውጭ ባለሀብቶች በእነዚህ ኩባንያዎች ውስጥ ሀብታቸውን ስራ ላይ የሚያውሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ አንዳንድ የግል የኢንቨስትመንት ፈንዶች (private equity funds) ከግል ባለሀብቶች ያሰባሰቡትን ገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኙ ኩባንያዎች ውስጥ ስራ ላይ በማዋል የኩባንያዎቹን አቅም በማሳደግ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ይህ የኢንቨስትመንት አማራጭ ለሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ኩባንያዎች አጋዥ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ይሁን እንጂ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ነባር ባለአክሲዮኖች የሚያወጡት አዲስ አክሲዮን በተፃፈበት ዋጋ (par value) እና በተሸጠበት ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት (premium) ግብር ሊከፈልበት የሚገባ በመሆኑ ባለሀብቶች አክሲዮን ከገዙበት ዋጋ ውስጥ የፕሪሚየሙ 30% ለግብር ክፍያ የሚውል መሆኑን ሲያውቁ ከፍተኛ ቅሬታ በማቅረብ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ይህ ቅሬታ ሀብታቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ እንዳያውሉ የሚያደርግ ስለሚሆን ችግሩን መፍታት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ መንግሥት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ (EIH) አቋቁሞ በከፍተኛ ደረጃ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ችግሩ ከግሉ ዘርፍ በተጨማሪ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ላይም አሉታዊ ተፅህኖ ስለሚኖረው የማሻሻያው አስፈላጊነት የበለጠ ይሆናል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

Samuel Gima Legal Consultant & Attorney

## 2. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች

በንግድ ሕግ አንቀጽ 435 እንደተደነገገው ኩባንያዎች ተጨማሪ ሀብት ስራ ላይ በማዋል የስራ እንቅስቃሴያቸውን ለማሳደግ በሚፈልጉበት ጊዜ ሊወስዱዋቸው ከሚችሉ እርምጃዎች አንዱ አዳዲስ አክሲዮኖችን ለገበያ በማዋል የኩባንያውን ዋና ገንዘብ ማሳደግ የሚያስችል ሀብት ማሰባሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚሁ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ መሰረት የኩባንያው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የኩባንያውን ካፒታል አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ለማሳደግ እና አዲስ የሚሸጡት አክሲዮኖች ከተፃፈባቸው ዋጋ በላይ በሆነ ገንዘብ እንዲሸጡ ከወሰነ በአክሲዮኖቹ ላይ በተፃፈባቸው ዋጋ (par value) እና በተሸጡበት ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት (premium) ወደመጠባበቂያ እንዲዘዋወር ሊደረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በንግድ ሕግ አንቀጽ 435(2) በግልጽ እንደተመለከተው አዲስ አክሲዮኖች ከተፃፈባቸው ዋጋ በላይ በሚሸጡበት ጊዜ ከዚህ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተካፋይ መሆን የሚችሉት አዲሶቹ አክሲዮኖች ከመሸጣቸው በፊት ባለአክሲዮን የነበሩት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በአዲስ አክሲዮን ላይ የተፃፈው ዋጋ የኩባንያውን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የሚውል ሲሆን በአክሲዮኖቹ ላይ ከተፃፈው ዋጋ በላይ አክሲዮኖችን በመሸጥ የሚገኘው ገቢ (Premium) ለነባር ባለአክሲዮኖች ጥቅም የሚውል ነው፡፡

## 3. የፕሪሚየም ገቢ ግብር የሚከፈልበት ስለመሆኑ

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 59 (1) አንድ ሰው ግብር የሚከፈልበትን ሀብት (የማይንቀሳቀስ ሀብት እና አክሲዮን/ቦንድ) በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ በተመለከተው መጣኔ መሰረት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

"ሀብትን ማስተላለፍ" የሚለው ሀረግ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 67 በሚገባ የተብራራ ሲሆን፤ በንዑስ አንቀጽ 2 ማናቸውም ሰው ከዚህ ቀደም ያልነበረን ሀብት የሌላ ሰው ሀብት እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ፤ ይህንን ያደረገው ሰው ሀብቱ በተፈጠረበት ጊዜ በባለቤትነቱ ስር የነበረን ሀብት ለሁለተኛው ሰው እንዳስተላለፈ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም አንድ ኩባንያ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ለገበያ ሲያውል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ኩባንያው በባለቤትነቱ ስር የነበሩ አክሲዮኖችን እንዳስተላለፈ የሚቆጠር በመሆኑ የዚህ አይነቱ የስራ እንቅስቃሴ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 59 ድንጋጌ ስር ስለሚወድቅ ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

## 4. አዲስ አክሲዮኖች በሚሸጡበት ጊዜ የሚገኘው ፕሪሚየም ከግብር ነፃ እንዲሆን የማድረግ አስፈላጊነት

በንግድ ሕጋችን እንደተደነገገው ኩባንያዎች አዲስ አክሲዮን በሚያወጡበት ጊዜ አክሲዮኑ ላይ በተፃፈው ዋጋ እና በተሸጠበት ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ተካፋይ

የፌደራል አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

መሆን የሚችሉት ነባር ባለአክሲዮኖች ናቸው። ይሁን እንጂ ነባር ባለአክሲዮኖች የመጠባበቂያውን ሂሳብ እስከሚከፋፈሉ ደረስ ኩባንያው በሀብቱ በመጠቀም የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅሙን ያሳድጋል። ይህ ሳይሆን የፕሪሚየሙ ዋጋ 30% ለግብር ክፍያ እንዲውል ቢደረግ የኩባንያውን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም በማሳደግ የትርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስቡ ባለሀብቶች የሚጠብቁትን ውጤት ስለማያገኙ ይሸሻሉ።

ይህ ደግሞ በካፒታል እጥረት ምክንያት በሙሉ አቅማቸው ለመስራት ያልቻሉ የአገራችን ኩባንያዎች ተጨማሪ አክሲዮን በመሸጥ ሀብት በማሰባሰብ በሙሉ አቅማቸው አምርተው ለአገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድ ያላቸውን ዕድል ያጠባል።

በሌላ በኩል አዲስ የሚቋቋሙ ኩባንያዎች በአክሲዩን ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ ግብር የማይከፈልበት በመሆኑ ባለሀብቶች አዋጭ ሆኖ ካገኙት የአዲስ ኩባንያን አክሲዮን መግዛት ሊመርጡ ይችላሉ።

5. <u>የሌሎች አገሮች ልምድ</u>

በአለማችን በርካታ አገሮች በካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር ይሰበስባሉ። የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር ከሚሰበሰብባቸው ገቢዎች አንዱ ከአክሲዮን ገበያ ውጪ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማህበራትን (private limited companies) አክሲዮን በመሸጥ የሚገኝ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ነው። የዚህ አይነት ኩባንያዎች ባለአክሲዮኖች ያላቸውን አክሲዮን ከተገዙበት ዋጋ በላይ በመሸጥ በሚያገኙት ገቢ ላይ ሁሉም አገራት የማስከፈያው መጣኔ ቢለያይም ግብር ያስከፍላሉ።

ነባር ኩባንያዎች ካፒታላቸውን ለማሳደግ ከሚያወጡት አዲስ አክሲዮን የሚያገኙትን ገቢ በተመለከተ አብዛኛዎቹ አገራት ይህንን ገቢ ሙሉ በሙሉ ከግብር ነፃ የሚያደርጉ ሲሆን፤ አንዳንድ አገራት ደግሞ የተወሰኑ ግብይቶችን ከግብር ነፃ ያደርጋሉ። ለምሳሌ በኬንያ እና ኡጋንዳ ነባር ኩባንያዎች ካፒታላቸውን ለማሳደግ ከሚሸጡት አዲስ አክሲዮን የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነፃ ነው። በሕንድ ነባር ኩባንያዎች አዲስ አክሲዮን በመሸጥ የሚያገኙት ፕሪሚየም ሌሎች ገቢዎች በሚል ርዕስ ስር ተመድቦ ግብር የሚከፈልበት ቢሆንም፤በህንድ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የሚገዙትን አዲስ አክሲዮን እንዲሁም ከፍተኛ ኪሳራን ሊያስከትሉ ይችላሉ በሚባሉ ፕሮጀክቶች ሀብቱን ስራ ላይ የሚያውል ኩባንያ ( venture capital ) የሚያገኘውን ገቢ ከግብሩ ነፃ ያደርጋሉ።

6. <u>ከግብር ነፃ የማድረግ ሥልጣን</u>

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 64 (2) የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ድንብ ለኢኮኖሚ፤ለአስተዳደራዊ ወይም ለማህበራዊ ምክንያቶች አንድን ገቢ ከግብር ነፃ ሊያደርግ እንደሚችል ይደነግጋል።

በመሆኑም በካፒታል እጥረት ምክንያት የስራ እንቅስቃሴያቸው የተዳከመ ድርጅቶች ተጨማሪ ካፒታል ለማሰባሰብ ከሚሸጡት አዲስ አክሲዮን የሚገኝ ገቢ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ምክር ቤቱ የዚህ ዓይነቱ ገቢ ከግብር ነፃ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።

ስለዚህ ከዚህ ጋር የተያያዘው ደንብ ስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድ ይህ አጭር መግለጫ ቀርቧል።